# ሻዕቢያ የሽብር አዝማችነቱ እስከመቼ ይቀጥል ይሆን?

ዘአማን በላይ

bzaman@yahoo.com

ድርጊቱ ለሰሚው የሚዘገንን ነው– ከመሰንበቻው በአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ መንግስት ቀጥተኛ ድጋፍ ሰጪነት በንፁሃን ቱሪስቶች ላይ የተፈፀመው አሳዛኝ ተግባር፡፡ እርግጥም ሰሞኑን "አምስት የውጭ ቱሪስቶች የኤርትራ መንግስት ባሰማራችው አሸባሪዎች ለህልፈተ-ህይወት ተዳረጉ፡፡ አንድ የጣሊያንና አንድ የሀንጋሪ ዜግነት ያላቸው ጎብኚዎችም በጥቃቱ የቆሰሉ ሲሆን፣ ሁለት ኢትዮጵያዊያንና ሁለት ኤርትራዊያን ደግሞ ተጠልፈው ተወስደዋል" የሚለውን እጅግ ዘግናኝ የዜና ዘገባን ያነበበ፣ ያዳመጠ ወይም የተመለከተ ሰብዓዊ ፍጡር ልቡ በሀዘኔታ መሰበሩ አይቀርም፡፡

በተለይም የሽብር ተግባሩ ዋነኛ ድጋፍ ሰጪና አቀነባባሪ የሆነው የአስመራው መንግስት መሆኑን የሰማ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፣ እንደ ዜጋ ድርጊቱ አእምሮውን መኮርኮሩ የግድ ነው፡፡ ምክንያቱም የኤርትራው መንግስት ዘግናኝ ክንዋኔ ሆን ተብሎ የሀገራችንን ገፅታ ለማጠልሸት የተከናወነ ስለሆነ ነው፡፡እናም በመዋቅር ብቻ በመንግስትነት ተደራጅቶ፣ በግብር ግን በእንዲህ ዓይነቱ ዘግናኝ እና መርህ-አልባ የጫካ ህግ እየተመራ የንጹሃንን ደም በማፍሰስ ላይ የተሰማራው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር፣ ዛሬም ድረስ የሳህል ተራራ ህጎች እንጂ፣ ዓለም አቀፍ ህጋጋት እንደማይገዙት በገሃድ ይገነዘባል፡፡

ታዲያ እኔም እንደ ማናቸውም ዜጋ በዚህ የሻዕቢያ እኩይ ሴራ ብዕሬን ከአፎቱ በመምዘዝ፣ ስለ አሳዛኝ ድርጊቱ ትንኮሳ አነሳሽ ምክንያቶችና የኤርትራ መንግስት የከሰረ ፖለቲካ ጥቂት ላወጋችሁ ወደድኩ፡፡ ግና የማነሳቸው ነጥቦች ለአንባቢዎቼ ግልፅ ይሆኑ ዘንድ፣ ‹‹የጥይት አረርን እንደ ዕጣን ካላሸተተ ውሎ የማያድረው፣ ግብረ- ሽበራን እንደ እለት እንጀራው የተያያዘውና ‹እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል› በሚል የሞኝ ብሂል ከራሱ ፃዕረ-ሞት ጋር ትንቅንቅ የሚያደርገው የአስመራው ቡድን፣ እንዲህ ዓይነቱን ትንኮሳ በተደጋጋሚ ለምን ይፈፅማል? እስከ መቼ ድረስ ነው በዚህ ሁኔታ አሸባሪዎችን ወደ ሀገራችን አስርጎ እያስገባ መልካም ገፅታችንን በማጉደፍ የሚቀጥለው? የሚሉና ሌሎች

ተዛማጅ ጥያቄዎችን በማንሳት ፈረንጆቹ ‹‹የከሰመ መንግስት›› (Failed state) የሚሉትን ስርዓት ቀቢፀ-ተስፋ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

## በትንኮሳ ላይ ትንኮሳ –ለምን?

የእርሳቸው ስልጣን የሚገድብ ወይም የሚቆጣጠር አንዳችም ኃይል የሌለባትን ኤርትራ በፈላጭ ቆራጭነት ረግጠው የሚያስተዳድሩትን የአቶ ኢሳያስ አካባቢያዊ ትርምስና ትንኮሳ እየደጋገሙ ለምን እንደሚፈፅሙ ከመግለፄ በፊት፤ ስለ የከሸፈው ስርዓታቸው ጥቂት ማውሳቱ ሁኔታውን አፍታትቶ ለመመልከት የሚጠቅም ይመስለኛል፡፡ እንደሚታወቀው ገና ከጅምሩ ሻዕቢያ የኤርትራን ነፃነት ከማረጋገጥ አልፎ፡ በዚያች ሀገር ማህበራዊ ፍትህን እንደማያነግስ በእርግጠኝነት የሚናገሩ ሰዎች በርካታ ነበሩ፡፡ እርግጥም የእነዚህ ግለሰቦች ‹‹ትንቢት›› ከመሬት ተነስቶ የተባለ አልነበረም– ከነባራዊ የድርጅቱና የመሪዎቹ ሁኔታ የተነሳ እንጂ፡፡ ለምን ቢባል፡ አነ አቶ ኢሳያስ ከሳህል ተራራ ጀምረው ይመሩበት የነበረው አካሄድ በጥገኝነት ላይ የተንጠለጠለ እንዲሁም በቀቢፀ ተስፋና በእልህ የሚዋተት የጦረኝነት አባዜ ስለነበር ነው፡፡

እንዲህ አይነቱ ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ደግሞ ‹‹ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም›› እንዲሉ ዓይነት በመሆኑ፤ ከኤርትራ ነፃነት በኋላ የስልጣን ኮርቻ ላይ የተቀመጠው የሻዕቢያ ቡድን በሀገር ውስጥ ህዝቡን ወደ ተሻለ ማህበረሰብ ከማራመድ ይልቅ፣ በላዩ ላይ ከፍተኛ የአፈና ቀንበር ነው የጫነበት፡፡ በሚከተለው ብልሹ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አመራርም ሀገሪቱን ወደማያባራ ቀውስ ውስጥ ከትቷታል፡፡

የኤርትራን ህዝብ እንደ ብረት ቀጥቅጦና እንደ ሰም አቅልጦ በመግዛት ላይ የሚገኘው የህግዴፍ ቡድን፤ በሀገረ-ኤርትራ ህገ-መንግስት እንዳይኖር፣ ነፃ ፍርድ ቤት እንዳይሰየም፣ ምርጫ እንዳይካሄድ፣ የግል ፕሬስ እንዳይፈጠር ባለፉት 20 ዓመታት ተግቶ ሰርቷል፡፡ የተጣባውን የጥገኝነት ተውሳክ በዚያች ሀገር ውስጥ እውን ለማድረግም በአደባባይ ወጥቶ መግለጫ እስከመስጠት የደረሰ ጉደኛ መንግስት ነው፡፡ ለዚህም የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ አምባገነኑ ኢሳያስ ለመገናኛ ብዙሃን ለኤርትራ ዴሞክራሲ፣ መድበለ ፓርቲ ስርዓትና ምርጫ የሚባሉት ነገሮች አያስፈልጓትም፡፡ አሁን ያለው ስርዓት ትክክለኛ አማራጭ ነው›› በማለት ዓለም የተቀበላቸውን ዴሞክራሲያዊ አሰራሮችን እንደ ተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ እንደሚፈሯቸው በግልፅ የተናገሩትን ሃቅ ማውሳት ይቻላል፡፡

ይህ ሁኔታም “ከነፃነት በኋላ ዲሞክራሲና ፍትህ የመጣል” ብሎ የጠበቀው የዚያች ሀገር ምስኪን ህዝብ፤ በአቶ ኢሳያስ የተደገሱለት ሀገሩ የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ምድረ-በዳ መሆኗን በመገንዘቡ፤ ለህግዴፍ የሰጠውን ይሁንታ ነፍጎ የፕሬዚዳንቱን ዕድሜ እንዲያሳጥርለት መመኘት እንዲጀምር አድርጎታል፡፡ ይህን ተከትለው ለአቅመ አዳም ያልደረሱና አዛውንቶች ሳይቀሩ የአቶ ኢሳያስን የግፍ በትር በመፍራት ሀገራቸውን ለቀው እየተሰደዱ ነው—‹‹ ማምሻም ዕድሜ ነው›› እንዲል የሀገራችን ሰው፡፡ በሻዕቢያ አመራር በትምህርት የማደግ ህልማቸው እንዲሞት የተደረጉት የሀገሪቱ ወጣቶችም ቢሆኑ ‹‹ ሳዋ፣ ኪሎማና ማይነፍሂ›› የተባሉ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ጣቢያዎች ከመግባት፣ ለኬላ ጠባቂዎች በመቶ ሺህ የሞቆጠር ናቅፋ በመስጠት የጎረቤት ሀገሮችን ድንበር እያቋረጡ በመሸሽ ላይ ይገኛሉ፡፡

እርግጥም ቀለምና ወረቀት አዋህደው ያቺን አዲስና ትንሽ ሀገር ሲያሳድጓት የሚችሉ ወጣቶች፤ ዛሬ በምሽግ ውስጥ እንዲውሉ ሲፈረድባቸው፣ በየወታደራዊ ማሰልጠኛው ጠብ-መንጃ ሲፈቱና ሲገጥሙ እንዲሁም ሰልፍ እንዲለማመዱ ሲደረጉ ብሎም ‹‹በዋርሳይ ይክአሎ›› ዘመቻ መንገድ፣ የጄኔራሎችን እርሻ እንዲያለሙ ጉልበታቸው ሲበዘበዝ ጨርቄን ማቄን ሳይሉ ከ“ከአቶ ኢሳያስ ሀገር” መጥፋታቸው የሚያስገርም አይሆንም፡፡ ታዲያ የዚህ ፅሁፍ አንባቢ ይህ ሁኔታ አቶ ኢሳያስን አጣብቂኝ ውጥ የከተታቸው “ቁጥር አንድ ድርጊት” ብሎ ሊመዘግብልኝ ይችላል፡፡

“ቁጥር ሁለት” አጣብቂኙ ደግሞ ከምጣኔ ሀብት አንፃር እንዲህ የሚገለፅ ነው፡፡ ‹‹የውሾን ነገር ያነሳ ውሾ ይሁን!›› እደሚባለው ሀገርኛ ይትብሃል፡ የኤርትራ ምጣኔ-ሀብት ከሞተ ውሎ አድሯል፡፡ በሻዕቢያ የሚመራው መንግስት ከጥገኝነት አስተሳሰብ ባሻገር ይህ ነው የሚባል የሚመራበት የልማት አቅጣጫ የሌለው በመሆኑ፡ የህዝቡ የኑሮ ሁኔታ በየጊዜው እንደ ካሮት እያሽቆለቆለ እንዲሄድ አድርጎታል፡፡ በዚያች ሀገር ውስጥ ማንኛውም ሸቀጥ የሚሸጠው በስርዓቱ ‹‹ህብረት ሱቆች›› በመሆኑ፤ ስለ ግል ባለሃብትና ስለ ነፃ ገበያ ስርዓት ማውራት እንደነውር የሚቆጠሩ ተግባሮች ናቸው፡፡

እናም ህዝቡ በነዚህ ሱቆች በራፍ ተኮልኩሎ የዕለት ምግቡን ይሸምታል፡፡ የመግዛት አቅም ያለው ውጭ ሀገር ዘመድ አሊያም ከሻዕቢያ ስርዓት ጋር ቁርኝት ያላቸው ጥቂት ዜጎች ሲሆኑ፤ አብዛኛው ህዝብ በችጋር አለንጋ እየተጠበሰ ነው፡፡ በ“ዓይኔን ግንባር ያድርገው” ዲፕሎማሲ የሚመራው የአስመራው አስተዳደር ምንም እንኳን ሁኔታውን

ቢክድም፣ ዓለም አቀፍ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአሁኑ ወቅት 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኤርትራዊያን በምግብ እጥረትና በረሃብ ላይ ናቸው፡፡ ይህም ከመላው የሀገሪቱ ህዝብ ግማሽ ያህሉ መሆኑ ነው፡፡

የአቶ ኢሳያስ መንግስት ህዝቡን ለዚህ ዓይነት አስከፊ ሁኔታ የዳረገበት ምክንያቶች በርካታ ናቸው፡፡የሀገሪቱን አንጡራ ሃብት ልማታዊ ተግባር ላይ ከማዋል ይልቅ፡ ለወታደሮቹ ትጥቅና መሳሪያ እንዲሁም ለፕሮፓጋንዳ ስራ የሚያወጣው ገንዘብ ብሎም ምሰራቅ አፍሪካን ለማተራመስ ለአሸባሪዎችና ለፀረ-ሰላም ኃይሎች ምልመላና ቅጥር ለስልጠና እና ለመሳሪያ ግዥ የሚያወጣውን ወጪ ከፍተኛ ከሚጠቀሱት ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት አድቅቆ ህዝቡን ለረሃብ በመዳረጉ፣ በሀገር ውስጥ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ኤርትራዊያንም የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ኃይሎችን በይፋ እየተቀላቀሉ ነው፤፡ ይህም በሀገር ውስጥ የአስመራው መንግስት የጎን ውጋት የሆነበት ሌላኛው አጣብቂኝ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

ይሁንና ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውን ሁለት አጣብቂኞች ለመከላከል የወሰደው ጎረቤቶቹን የማሸበርና የማተራመስ እርምጃ ምንም አልፈየደለትም፡፡ የሀገር ውስጥ ችግሩን በማተራመስ ለማካካስ ቢሞክርም፣ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ቤተክርስቲያን እንደገባች ውሻ በማዕቀብ ናዳ ከመባረርና እንደ ደሴት ከመገለል ውጭ ያስገኘለት እርባና የለም፡፡ የህዝቡን ውስጣዊ ብሶት ለማዳፈንና አቅጣጫ ለማስቀየር በአገዛዝ ዘመኑ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከአራት ጎረቤቶቹ ጋር ቢጋጭም፣ ዘዴው የሰመረለት አይመስልም– ዛሬም ድረስ ከህዝቡ ጋር ሆድና ጀርባ ነውና፡፡

በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ እምነት፡ የኤርትራ መንግስት በትንኮሳ ላይ ትንኮሳ እያከታተለ የሚፈፅምበት ዋነኛው ምክንያት፣ እንደ እሳተ-ገሞራ ለመፈንዳት የተቃረበውን ውስጣዊ ተቃውሞ ያረገበ መስሎ ስለሚታየው ነው፡፡ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ የሚልካቸው እንደ ኦነግ፣ ኦብነግና ግንቦት 7 የመሳሰሉ አሸባሪዎች ውጤት ሊያመጡለት ስላልቻሉ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቅጥረኞችን በማሰልጠንና በማስታወቅ የሀገራችንን መልካም ስም ለማጉደፍ በቀቢፀ- ተስፋ እየተራወጠ ይገኛል፡፡

የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ የቱሪስት መስህብ በሆነው አርታሌ አካባቢ የውጭ ዜጎችን አሳፍኖ ያስወሰደው እና ልክ የዛሬ ዓመት የአፍሪካ ህብረት 16ኛ የመሪዎች ጉባኤን በማደናቀፍ ሀገራችN ውስጥ ሰላም የሌለ ለማስመሰል የኦነግ ጅሌዎቹን ልኮ በኢትዮጵያ ህዝብና በፀጥታ ሀይሎች ጥረት የከሸፈበት የአስመራው አስተዳደር፣ እኩይ ሴራውን የቤተክርስቲያን ስዕለት ያለበት ይመስል በዓመቱ በአርታሌ አካባቢ መድገሙ "ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል" ዓይነት ፖለቲካዊ አንድምታ ያለው ነው፡፡ እርግጥም በቀቢፀ-ተስፋ የተሞላው የሻዕቢያ አንድምታ ይህን ይመስላል፡፡ …

የኤርትራ መንግስት ተላላኪዎችንና ቅጥረኞችን እየፈለፈለ፣ አንድን ሀገር ተተናሎ ሲያበቃ በምላሹ ሀገራቱ ጣታቸውን ወደ እርሱ ሲቀስሩ፣ ህዝቡን "እገሌ የሚል ሀገር ሊወርህና ነፃነትህን ሊያሳጣህ ነው" በሚል ፕሮፓጋንዳ ለማወናበድና ለጊዜውም ቢሆን ለህዝባዊ ተቃውሞው ፋታ መውሰጃ ይጠቀምበታል፤፡ በተለይም ራሱ የተከተለው ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ አካሄድ መልሶ ራሱን ጠልፎ እንደጣለው ባለመገንዘቡ፣ ለውድቀቱ ምክንያት ኢትዮጵያ እንደሆነች አድርጎ በማቅረብና በሀገራችን ላይ በትንኮ ላይ ትንኮ እየፈጸመ መቀጠልን እንደ አማራጭ ወስዷል፡፡

ግና ወዳጆቻቸው የነበሩትን ሆስኒ ሙባረክንና ኮሎኔል ሙአመር ጋዳፊን ጠራርጎ የወሰዳቸው ህዝባዊ ማዕበል መሆኑን የማታ ማታም ቢሆን የተረዱት የኤርትራው አምባገነን፣ እስከ መቼ ድረስ ይሆን በዚህ የሽብር ካርድ መንበረ ስልጣናቸውን እያስጠበቁ የሚዘልቁት? የሚል ጥያቄ በበርካታ ወገኖች ዘንድ በመመላለስ ላይ ይገኛል፡፡

## እስከመቼ በሽብር አዝማችነት?

አስመራው መንግስት የሽብር አዝማችና አጋፋሪ ሆኖ የቀጠለው በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት አከርካሪው ተመትቶ ከተሰባበረ በኋላ ነው ማለት ይቻላል፤፡ በኤርትራ ውስጣዊ አቅምና ፀጋዎች ከመተማመን ይልቅ፣ የጎረቤት ሀገሮችን ሃብት በጥገኝነት ዓይኑ ያማትር የነበረው የአቶ ኢሳያስ ቡድን፣ ማጣፊያው ሲያጥርበት በአንድ ወቅት "ሀገራችንን ሲንጋፖርና ታይዋን አድርገን ምርቶቻችንን ወደ ውጭ እንልካለን" እንዳላለ፡ ዛሬ ሽብርንና ትርምስን አስመራ ውስጥ እያመረተ ወደ ጎረቤት አገር መላክ ሁነኛ ስራው ሆኗል፤፡ በዚህም የሱዳንና የጅቡቲ ‹‹ አማጺዎችን›› እንደ ሀገር ውስጥ ምርት በየወታደራዊ ማሰልጠኛW እያመረተ በመላክ ላይ ይገኛል፤፡ ራሳቸውን ኦነግ፣ ኦብነግ፣ ግንቦት 7 ወዘተ

እያሉ የሚጠሩ የሀገራችንን አሸባሪዎችንም እየመለመለ፣ እያሰለጠነ፣ እያስታጠቀና እያሳረገ ለማስገባት ሞክሮ ባይሳካለትም፤ የጥፋት እጆቹን እስካሁን ድረስ ከኢትዮጵያ ላይ ሊያነሳ አልቻለም፡፡

ሻዕቢያ በሀገረ ሶማሊያ ውስጥ አክራሪዎችን ከማሰልጠንና ከማስታጠቅ አልፎ ወታደሮቹን ልኮ እስከ መዋጋት ደርሷል፡፡ በዚህም የገዛ ዜጎቻቸውን እጅና እግር የሚቆርጡ አሸባሪዎችን እየረዳ ያቺን ሀገር የደም ምድር በማድረግ ረገድ የበኩሉን አሉታዊ ድርሻ ተጫውቷል፡፡ በቅርቡም አል-ሸባብ ለተሰኘው የሽብር ቡድን የስልጠና፣ የሎጀስቲክስና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የግብረ-ሽብራ ፊታውራሪነቱን በጠራራ ፀሀይ አረጋግጧል፡፡

ከሽብር ተግባር ጋር የካቶሊክ ጋብቻ የፈፀመው የአቶ ኢሳያስ መንግስት፤ እኩይ ሴራውን በምስራቅ አፍሪካ ተወዳድሮ ያገኘው ‹‹ክፍት የስራ ቦታ›› ይመስል ‹ሞቴን ከአሸባሪዎች ጋር ያድርገው› ብሎ ተገዝቶ ከማለ ሰነባብቷል፡፡ ታዲያ ይህን ተግባሩን በአሁኑ ወቅት እያደረገ ካለው አፍራሽ ድርጊት አኳያ ስንመዝነው፤ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከአንድም ሁለቴ ከጣለበት ማዕቀብ እንኳን የሚማር አይመስልም፡፡

እንደሚታወቀው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት የኤርትራ መንግስት በኃይል ከያዘው የጅቡቲው‹‹ራስ  ዱሜራ›› ግዛት እንዲወጣ እንዲሁም የሶማሊያ አሸባሪዎችንና ጽንፈኞችን መርዳቱን እንዲያቆም ሲጠይቀው፣ ‹እምቢኝ አሻፈረኝ› በማለቱ የመጀመሪያውን የመሳሪያ ዝውውር፣የባለስልጣናት ጉዞና ሌሎች ማዕቀቦችን ጥሎበታል፡፡ ይሁንና ዓለም አቀፉን ህግና ስርዓት በይፋ የሚዘልፉት አቶ ኢሳያስ፣ የፀጥታውን ምክር ቤት ማዕቀብ ከቁብ ሳይቆጥሩ በሽብር አዝማችነታቸው እነሆ ዛሬም ቀጥለውበታል፡፡

ሆኖም የምስራቅ አፍሪካ የልማት በየነ መንግስታት ባለስልጣን (ኢጋድ) እና የአፍሪካ ህብረት የአስመራው ቡድን የቀጠናው ‹‹ተናዳፊ ኃይል›› መሆኑንና ያካባቢውን ሰላምና መረጋጋት ማደፍረሱን ለጸጥታው ምክር ቤት በማመልከታቸው፤ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የኤርትራንና የሶማሊያን ሁኔታ የሚያጣራ አካል መድቧል፡፡

አጣሪ ቡድኑም ባደረገው ጥልቅ ጥናት የአስመራው አስተዳደር የአካባቢው ሰላም ጠንቅ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የህግዴፍ መንግስት ቀደም ሲል የተጣለበትን የመሳሪያ ዝውውር ማዕቀብ በመተላለፍ ለአል-ሸባብ መሳሪ እንደሚያቀብል፣ የጎረቤት ሀገሮችን ፀረ-

ሰላም ኃይሎችና አሸባሪዎችን ጉያው ስር ወሽቆ ሀገራቱን እንደሚያውክ የቡድኑ ሪፖርት አረጋግጧል፡፡ ናይሮቢ የሚገኘው የኤርትራ ኤምባሲ ተቀዳሚ ስራው ድፕሎማሲ ሳይሆን በሃዋላና በደሃብሺል የገንዘብ ማዘዋወሪያዎች አማካኝነት በአል-ሸባብ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም ለሽብተኛ ቡድኖች ሽፋን የመስጠት ተግባር መሆኑን አጣሪ ቡድኑ ደርሶበታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም፤ የዛሬ ዓመት ገደማ በመዲናችን አዲስ አበባ የተካሄደውን የአፍሪካ ህብረት 16ኛ ልዩ ጉባኤን በግብረ-ሽበራ ተግባር ለማወክ የአቶ ኢሳያስ መንግስት የኦነግ ጀሌዎችን ከኤርትራ ወደ አዲስ አበባ ሰርገው እንዲገቡ ማድረጉ በቡድኑ ሪፖርት ላይ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ይህን ሁኔታ በአፅንኦት የተመለከተው የጸጥታው ምክር ቤትም ህዝቡን በማይጎዳ መልኩ በኤርትራ መንግስት ባለስልጣናት የሽብር አዝማችነት ላይ ሁለተኛውን ማዕቀብ በሽልማት መልክ ‹‹እነሆ!›› ብሏቸዋል፡፡ ይህ በአስመራው አስተዳደርና በሽብር ተግባር ላይ የተሰማሩ ሹማምንቶቹ ላይ ተለይቶ የተጣለው ማዕቀብ የግብረ- ሽበራ ተግባሩን ሊቀንሰው ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

አቶ ኢሳያስ ግን ለእነዚህ ዓለም አቀፍ ውግዘቶች ቦታ ከመስጠት ይልቅ፤ ዲፕሎማሲያዊ መንገድን አሽቀንጥረው በመጣል ዓለምን ለማሸበር ቆርጠው የተነሱ ይመስላል፡፡ ለዚህም ሳይሆን አይቀርም በአፋር ክልል አርታሌ አካባቢ ያለውን የተፈጥሮ መስህብ ለመጎብኘት የሄዱ ሃያ ሰባት የሚሆኑ የአሜሪካ፣ የጀርመን፣ የኦስትሪያ፣ የጣሊያን፣ የሃንጋሪና የሌሎች ሀገር ቱሪስቶች ላይ በአሳቻ ሰዓት ጥቃት ለመክፈት የፈለጉት፡፡

ይሁንና የአስመራው አምባገነን መሪ በጀሌዎቻቸው አማካኝነት የአንድን ሉዓላዊት ሀገር ድንበር ጥሰው ሽብር የሚፈፅሙበት አካሄድ አንድ ቦታ ላይ መገታት ይኖርበታል፡፡ የኤርትራ መንግስት በባህሪው ለትዕግስት ቦታ የሚሰጥ ባለመሆኑ፤ ከዚህ ፀያፍ ተግባሩ እንዲታቀብ የመንግስታችን የተለመደው አስተዋይነትና ብቃት ያለው የአመራር ክህሎት ታክሎበት ተመጣጣኝ እርምጃ ያስፈልገዋል ባይ ነኝ፡፡

በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ እምነት አቶ ኢሳያስ የባሩድ ሽታን እንደ ሀሺሽ “የመጀንጀን” ሱስ የተጠናወታቸው በመሆኑ፣ እርሳቸው “በሚገባቸው ቋንቋ” አናግሮ ተገቢ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ አቅሙም ይሁን ብቃቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመሰከረለት እንዲሁም ሻዕቢያ ጠንቅቆ እንደሚያውቀው የምሱን የሚሰጠው ሰራዊታችን

ሁሌም ዝግጁ መሆኑ ግልፅ ነው። እናም ነገሩ "ምከረው ምከረው እምቢ ያለ እንደሆን መከራ ይምከረው" መሆኑን የአስመራው ቡድን ማወቅ ያለበት ይመስለኛል።

## የሽብር ጥቃቱ አንድምታዎች

የኤርትራ መንግስት በተላላኪዎቹ አማካኝነት ሰሞኑን በንፁሃን ቱሪስቶች ላይ ያደረሰው ጥቃት በቀጥተኛ የሽብር ፈጠራ ተግባራት ውስጥ መዘፈቁን የሚያመላክት ብቻ ሳይሆን፤ ያልተሳካለት የቀጠናው አውራ የመሆን ህልም ሀገራችንን በማጠልሸት ለማካካስ በቀቢፀ ተስፋ እየተወራጨ መሆኑን ጭምር የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም፤ የአስመራው አስተዳደር ‹እንዴ እኔ በኢኮኖሚ የደቀቅኩ ፣ከዓለምም የተገለልኩ ስለሆነ ከዚህ ወዲያ ምን ይመጣብኛል' ከሚል ተስፋ መቁረጥ በመነጨ 'እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል' የሚል ብሂልን እየተከተለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ታዲያ እነዚህን አንድምታዎች አንድ በአንድ አፍታትተን መመልከት፤ አቶ ኢሳያስ ሰርጎ ገቦቻቸውን አስርገው በማስገባት ለምን እንዲህ ዓይነቱን ዘግናኝ ድርጊት ለመፈፀም እንደተነሳሱ ለመረዳት ያግዘናል፡፡

እንደሚታወቀው ሻዕቢያ በሳህል ተራራዎች ውስጥ በመሸገበት ወቅት መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ያገኘው የነበረው ዳረጎት፤ ስልጣን ከያዘም በኋላ ቢሆን ይህን መሰሉን ገቢ የአካባቢው ሀገሮች አድራጊ ፈጣሪ ሆኖ ለማግኘት ይቋምጥ ነበር—ፍላጎቱ ከንቱ ቅዠት ሆኖ ቀረ እንጂ፡፡ እናም በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚንቀሳቀስ አንዳንድ ሀገራትን በቀጣናው አውራ ስለሆንኩ፣ ከእኔ ጋር ጥሩ ግንኙነት ብትመሰርቱ ትጠቀማላችሁ በማለት ኪራይ ለመሰብሰብ ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም፡፡ ግና ምን ያደርጋል?! ከኢትዮጵያ ጋር ያደረገውና በገዛ እጁ የከፈተው ጦርነት ራሱን ሰቅሎ ከነበረው የህልም ዓለም ማማ ላይ እንዲወርድ አደረገው፡፡ በዚህም እስከዛሬ ድረስ ሀገራችንን በደመኛ ጠላትነት ፈርጆ፤ ፀረ-ሰላምና አሸባሪ ኃይሎችን እንደ አሮጌ ዕቃ ከወዳደቁበት ለቃቅሞ እያነሳ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ መልካም ገፅታዋን ማጥቆር እምቡር እምቡር እያለ ነው፡፡

ነገሩን ከእነ አቶ ኢሳያስ ቀሽም ስሌት አኳያ ስንመለከተው፤ 'ኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረጉ ዓለምና አህጉር አቀፍ ጉባኤዎችን ማደናቀፍ እንዲሁም የውጭ ዜጎችን ማፈንና መግደል ሀገሪቱ ሰላም እንደሌላት አድርጎ ለማስመሰል ይጠቅማል› የሚል ሆኖ

እናገኘዋለን፡፡ ለዚህም ነው አምና በኤርትራ መንግስት የውጭ ዘመቻዎች ዳይሬክቶሬት የተፀነሰው፣የተቀነባበረው፣የተደገፈውና የተመራውን የአሸባሪው የኦነግን የጥፋት ተልዕኮ ለማስፈፀም ከተመደቡት ጀሌዎች ውስጥ አንዱ የሆነው ኡመር እንድሪስ መሐመድ እንዲህ ሲል የመንግስታቱ ድርጅት ለመደበው አጣሪ ቡድን የተናገረው። ….

> *"…ብርጋዲየር ጄኔራል ጠዓመ ላፕ ቶፕ ኮምፒዩተሩን ከፈተው።የኢራቅ ሰርጎ ገቦች እንዴት አድርገው ከባድ ፈንጂዎችን እንደሚያቀነባብረ በቪዲዩ ምስል አሳየኝ።እርግጥ የእርሱ ፍላጎት እኔን ማነሳሳት ነው።…ከዚያም ኮምፒዩተሩን በመዝጋት 'አዲስ አበባን ባግዳድ እናደርጋታለን፣በዚህም ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም እንደሌለ ለአፍሪካውያን እናሳያለን አለኝ።…"*

አዎ! ይህ ምስክርነት እርግጥም የኤርትራ መንግስት በአፍሪካ ቀንድ የሚያደርገውን የውጭ ሽብር ዘመቻን በዋነኝነት በሚያዘው ብርጋዲየር ጄኔራል ጠዓመ ጎይትኦም ክንፉ አማካኝነት የሀገራችንን በጎ ገፅታ ለማጠልሸት ምን ያህል ቆርጦ እንደተነሳ የሚያረጋግጥ ነው። ሰሞነኛው በቱሪስቶች ላይ የተሰነዘረው ጥቃት የዚሁ ፍላጎቱ ተቀጥላ ነው፡፡ ምክንያቱም የአቶ ኢሳያስ መንግስት በሌለ ነባራዊ ሁኔታው ‹‹የቀጣናው ወሳኝ ኃይል›› ሆኖ የመታየት የቀን ቅዠቱን በዚህ ዓይነቱ ዘግናኝ ተግባር ያደሰ ስለሚመስለው ነው— እርግጥም ድርጊቱ ‹‹ጅብ የማያውቁት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ›› አለ የሚለውን ብሂል ያስታውሰናል፡፡

እናም ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የአስመራውን መንግስት በግብረ-ሽብራ ምግባሩ በግልጽ "የቀጣናው አዋኪ ነህ" በሚል ቋንቋ ፈርጆታል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን፤ የአስመራው መንግስት ያሻውን የሽብር ድርጊት ቢፈፅም፤ የሀገራችን መንግስትና ህዝብ እያስመዘገቡ ካሉት ፈጣን ልማትና ዕድገት አንድም ስንዝር ወደ ኋላ የሚሉ አለመሆናቸውን ጊዜው ሳይረፍድበት ቢገነዘብ መልካም ይመስለኛል፡፡

ምንም እንኳን የሻዕቢያው ሰሞነኛ የሽብር ጥቃት በዚህ ወር ውስጥ ከሚካሄደው የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ጋር ለማገጣጠም የታለመ ቢሆንም፤ አፍሪካዊያን ትናንትም ሆነ ዛሬ ነፃነቷን ጠብቃ የኖረችውን ሀገራችንን አስተማማኝ ሰላም ይረዳሉ፡፡ በመሆኑም

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት የህብረቱ ስብሰባዎች ያለምንም የፀጥታ ችግር እንዲከናወኑ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ በብቃት እንደሚወጡ ያምኗቸዋል፡፡ እናም የኤርትራ መንግስት በርካታ ኪሎ ሜትሮች ላይ የፈፀመው ‹‹የፈሪ ዱላ›› ዓይነት የሞኝ ሴራ ከመሳለቂያነት ውጪ የሚያተርፍለት አንዳችም ጥቅም አይኖርም– ምንም እንኳን የሻዕቢያ ነገር ‹‹ቅና ያለው ሰው በምንትስ ይቀናል›› እንዲሉ ቢሆንም፡፡

በዚህ ጽሁፍ አቅራቢ እምነት የአቶ ኢሳያስ መንግስት ያልተገነዘበው ትልቅ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም እርሱ በየጊዜው ለሚጎነጉነው የሽብር ሴራ እንደ ነብር ጭራ ከያዘው ፈጣንና ተከታታይ ልማታዊ ዕድገት የሚዛነፍ መንግስትም ይሁን ህዝብ አለመኖሩን ነው፡፡ የሀገራችን ህዝብና መንግስት የሻዕቢያ ኢኮኖሚ በየጊዜው ከድጡ ወደ ማጡ እየተንሸራተተ መግባቱን ብቻ ሳይሆን፣ እንደ መንግስትም ህልውናው አጠራጣሪ ሁኔታ ላይ መድረሱን ይረዳሉ፡፡ አርግጥም ከራሱ የሞት መንፈስ ጋር ትንቅንቅ እያደረገና በቀቢፀ-ተስፋ ቀሪ ዘመኑን ለመዳከር የወሰነ መንግስትን እብደት እያዩ እርሱ በመረጠው ጎዳና ላይ አብረውት አይሮጡም– የራሳቸው የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ማማን (Track) ተከትለው ይነጉዳሉ እንጂ፡፡

ይሁንና ይህ ማለት ግን፣ የጀመሩትን የዕድገት ጎዳና ለማደናቀፍ ሀገራቸው ውስጥ በማን አለብኝነት የሽብር ተግባርን አከናውናለሁ የሚል ኃይልን ዝም ብለው ያያሉ ማለት አይደለም፡፡ ከብዙ ትዕግስት በኋላ፣ ሰላማቸውን በማስጠበቅ ልማታቸውን ያለምንም እንከን ለማከናወን አስፈላጊ ነው ያሉትን እርምጃ ከመውሰድ ወደ ኋላ እንደማይሉ መገንዘብ ይበጃል፡፡

ለዚህም ይመስለኛል የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጥቃቱን አስመልክቶ ‹‹ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የኤርትራ መንግስትን ህገ-ወጥነት ለማስቆም እርምጃ የማይወስድ ከሆነ፣ መንግስት የሽብር ተግባሩን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስቆም አስፈላጊ ሆኖ የተገኘውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል›› በማለት መግለጫ ያወጣው፡፡ እናም የአስመራው የሽብር መሪ አቶ ኢሳያስ ጆሮ ካላቸው መስማት የሚገባቸው ወቅት አሁን ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም እየፈጸሙ ያሉት አደገኛ ተግባር ‹‹ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ፣ አሊያ ግን ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል›› እንዲሉት መዘዙ የከፋ ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡

## የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ግዴታስ?

በአሁኑ ወቅት ዓለም የኤርትራን መንግስት የሽብር አዝማችነት በአግባቡ ተረድቷል፡፡ ለዚህም ከአንዴም ሁለቴ ማዕቀብ የጣለበትን አግባብ በእማኝነት ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይሁንና የአስመራው አስተዳደር ከሚፈፅማቸው ከባድ ጥፋቶች አኳያ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጠንካራ እርምጃዎችን በአፋጣኝ ወስዷል ብሎ ለመናገር የሚከብድ ይመስለኛል፡፡ ይህ ሁኔታም አቶ ኢሳያስ ከጫካ ይዘውት በመጡት ህግ እንጂ፣ በዓለም አቀፉ ህግ እንዳይመሩና ነባሪያዊ ባህሪያቸውን ይዘው እንዲቀጥሉ አድርጓል፡፡ እርግጥም የዓለም አቀፉ ማህበረተሰብ፣ ያለ ህግ በጋጠ-ወጥነት ቀጣናውን የሚያተራምሱትን ግለሰብ እንዲህ ‹‹እሹሩሩ›› የሚላቸው ለምን እንደሆነ ለማንም ግልፅ የሚሆን አይመስለኝም፡፡

እንደሚታወቀው አቶ ኢሳያስ ሲያሻቸው የመንግስታቱን ድርጅት ይዘልፋሉ፣ በል ሲላቸው ደግሞ ‹‹ድርጅቱ ዋጋ ቢስ ነው›› በማለት ሲያጣጥሉትና ሊሳለቁበት ይከጅላሉ፡፡ በድርጅቱም ህግጋቶች ላይ በየጊዜው በሚሰጡት መግለጫ በገሃድ ንቀታቸውን አንፀባርቀዋል፡፡አልፎ አልፎም ቢሆን በተመድ ስብሰባ ላይ እየተገኙ በንግግራቸው የድርጅቱ መዋቅር አስተካካይ ሆነው በመቅረብ የሽሙጥ ታሪክ ድርሳናቸውን ያንበለብላሉ፡፡ እነዚህ ተግባሮቻቸው የሚያሳዩት ነገር ቢኖር፣ ወይ ተመድ ትክክል አይደለም አሊያም ደግሞ ሰውዬው ከዓለም አስተሳሰብ በተፃራሪው የሚጓዙ ግለሰብ ናቸው፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፣ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ይሳሳታል ብሎ መገመት የዋህነት ነው፡፡ እናም ችግሩ ያለው በምስራቅ አፍሪካ የኦሳማ ቢን ላዲንን የሽብር ፈለግ ተከትለው እየተንቀሳቀሱት ባሉትና የሚናገሩትን እንኳን በማያውቁት በአስመራው ቁንጮ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሰላማዊን መንገድ ከሚከተለው የዓለም ህብረተሰብ አፈንግጠው በራሳቸው ‹‹የሽብር ምህዋር›› ዙሪያ የሚሽከረከሩትን እኚህን አምባገነን አፋጣኝና ተገቢ እርምጃ ሊወስድባቸው ይገባል፡፡ አሊያ ግን ድርጅቱ የተቋቋመበትን የሀገራቱን ሰላም የማስጠበቅ ግዴታውን በአግባቡ ተወጥቷል ለማለት የሚከብድ ይመስለኛል፡፡

እርግጥ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ‹‹የኢትዮጵያ መንግስት ለሰላም የቆመ፣ በዓለም አቀፉ ህግና ደንብ የሚመራ ብሎም ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ብቃት ያለው

ነው›› በሚል ግንዛቤ ነገሮችን ሊመለከት ይችላል፡፡ ምንም እንኳን ይህ እሳቤ ትክክል ቢሆንም፤ የዓለምን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የተቋቋመው፣ የፀጥታው ምክር ቤት እንደ ኢትዮጵያ ያለ ለዓለም አቀፉ ህግ ተገዥ የሆኑ ሀገራትን ፀጥታ የማስከበር ግዴታ እንዳለበት መዘንጋት ያበት አይመስለኝም፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት እስከዛሬ ድረስ የአስመራውን አስተዳደር የጠብ-አጫሪነት ተግባር ዓለም አቀፉ ህግ የሚቅደውን አግባብ ተከትሎ ችግሩን ለመፍታት ጥረት አድርጓል፡፡ ሌላው ቀርቶ ቀደም ሲል የጠቀስኩትን 16ኛውን የአፍካ ህብረት የመሪዎች ልዩ ጉባኤን ለመበጥበጥ የኤርትራ መንግስት የሞከረውን ፍጹም ፀረ-ህዝብ ድርጊት እንኳን ለዓለም አቀፉ ማህበረተሰብ አሳልፎ ከመስጠት ውጪ የወሰደው እርምጃ የለም፡፡ ይህም መንግስት ምን ያህል በህግ እና በህግ ብቻ እንደሚገዛ በተግባር አረጋግጧል፡፡

በአንፃሩ ደግሞ ዓለም አቀፉ ማህበረተሰብ በተለይም የፀጥታው ምክር ቤት የዚህን የሽብር አዝማች መንግስት ማንነት እያወቀ፤ ከማዕቀብ በዘለለ የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ ከእኩይ ተግባሩ እንዲቆጠብ አላደረገም፡፡ በመሆኑም በእኔ እምነት ምክር ቤቱ ሙሉ በሙሉ ግዴታውን መወጣቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

የኤርትራ መንግስት ምስራቅ አፍሪካን እንዲያሸብር "ህጋዊ እውቅና" የተሰጠው ይመስል በማን አለብኝነት የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ዜጎች ሲያሸብር፤ በተለይም የኢትዮጵያን ሰላም ለማደፍረስ እየጣረ ባለበት በአሁኑ ወቅት ጉዳዩን በባይተዋርነት መመልከቱ የተጣለበትን ዓለም አቀፍ ግዴታ ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ‹‹በጥባጭ እስካለ ማን ጥሩ ይጠጣል›› እንዲል የሀገራችን ሰው፤ ምክር ቤቱ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር በላካቸው ጀሌዎቹ አማካኝነት ከተለያዩ የዓለም ማዕዘናት የመጡትን ቱሪስቶች መግደሉን፣ማቁሰሉና ማፈኑን ተረድቶ አደብ የሚያስገዛ እርምጃ የሚወስድበት ጊዜ ገና የረፈደ አይመስለኝም፡፡

እርግጥ እንደ ማንኛውም ሀገር መንግስት የኢትዮጵያ መንግስትም በሉዓላዊ ግዛቱ ውስጥ ባዕዳን በሽብር ተግባር እንዳሻቸው ሲፈነጩ እጅና እግሩን አጣጥፎ ሊቀመጥ አይችልም፡፡ ምክንያቱም በዓለም አቀፉ ህግ መሰረት ራሱን የመከላከል ህጋዊ መብት ስላለው ነው፡፡ ለዚህም ነው የሀገራችን መንግስት ይህን መብቱን በመጠቀም ዓለም አቀፉ ማህበረተሰብ ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ፤ራሱን መከላከሉ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በተግባር

እንደሚፈፅመው በይፋ ያሳወቀው፡፡ ግና ይህ እንዳይሆን እና ጦርነት እንዳይቀሰቀስ የመንግስታቱ ድርጅት በኤርትራ መንግስት ላይ የማዳግም እርምጃ በመውሰድ ግዴታውን መወጣት ያለበት ወቅት አሁን ይመስለኛል፡፡